# በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት የ2008 ዓ.ም.
# የ4ኛው ሩብ አመት እና የአመቱ ማጠቃለያ የክንውን ሪፓርት

## ክፍል አንድ፡ ገለጻ

### 1. መግቢያ

ሐረማያ ዩኒቨርስቲ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉትከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ቀደምትና አንጋፋ ከሆኑት አንዱ ሲሆን ላለፉት 60 ዓመታት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራትና ሀገራዊ ጠቀሜታ ያስገኙ ዘርፈ-ብዙ የምርምር ውጤቶችን በማፍለቅ ሲሰራ ቆይተል፡፡ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ስርጸትቢሮየዩኒቨርሲቲዉን የምርምርና የምርምር ውጤቶች ስርጸትን በማስተባበርና በመከታተል ዩኒቨርሲቲው በምርምር ስራና ውጤት የላቀ ደረጃ እንዲደርስ ያላሰለሰ ጥረት በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተላይም በግብርናው የምርምርና ስርጸት ዘርፍ ዩኒቨርሲቲው ፊር ቀዳጅ ሲሆን በዘርፉም በርካታ ፈርጥ ተመራማሪዎችን ያፈራና በርካታ የምርምር ውጤቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅና በማሰራጨት የማህበረሰቡ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ወደ 135 የሰብል ዝርየዎችንና ሌሎች በርካታ ቴክኖሎጂዎችን አመንጭቶ በጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በርካታ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችን በዓለም-አቀፍ ድርሳናትና መጽሀፍት መልክ አሳትሟል፡፡

ከ1980ዎቹ ጀምሮ ዩኒቨርሲቲው ከግብርና በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የትምህርት መስኮች መከፈትን ተከትሎ የምርምርና ስርጸት ዘርፉም ያደገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በ 6 የምርምር የትኩረት መስኮች ስራውን እያካሄደ ይገኛል፡፡ እነኚህ የምርምር ትኩረት መስኮች የዩኒቨርሲቲውን በመማር-ማስተማርና ምርምር እንዲሁም በማህበረሰብ አገልግሎት ተሳትፎ ለመላቅ ያስቀመጣቸውን የትኩረት መስኮችና ራዕዩን ለማሳካት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

የምርምርና ስርጸት ቢሮ የተጠቀሱትን የትኩረት መስኮች ለማሳካት በምርምር ቡድኖችና አጋርነት፣ በምርምር ስርጸትና ህትመት፣ እና በምርምር ፋሲሊቲዎች ዳይሬክቶሬቶች ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ለ6ቱ የምርምር የትኩረት መስኮች ስድስት መሪዎች ተመድበው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በዚህም መሰረት የምርምር ቡድኖችና አጋርነት ዳይሬክቶሬት የምርምር ስራዎችን የማስተባበር፣ የመከታተል፣ ድጋፍ የመስጠት ስራና የዩኒቨርሲቲውን የምርምር ስራ ከሌሎች ባለድርሻ አካላትና የምርምር ሀገር ዓቀፍና አለም ዓቀፍ ድጋፍ አድራጊ ድርጅቶች ጋር የማስተሳተር ስራዎችን ያከናውናል፤የምርምር ስርጸትና ህትመት ዳይሬክቶሬት የምርምር ውጤቶችን፣ እውቀቶችን፣ ቴክኖሎጂዎችንና መልካም

አሰራሮችን ለተጠቃሚው ማድረስ፣ እንዲደርሱ ማድረግ እና የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎችና የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የምርምር ግኝቶች በምርምር ድርሳናት፣ በመጻኅፍትና በመጽሄፍ መልክ፤ በፕሮሲዲንግ እና በሌሎች የህትመት አይነቶች እንዲታተሙ የማበረታታት፤ የማሳተምና የማሰራጨት ስራዎችን ያከናውናል፤ የምርምር ፋሲሊቲዎች ዳይሬክቶሬት የምርምር ፋሲሊቲዎችን የማስተዳደር፤ የማስፋፋት፤ የማዘመንና በአግባቡ እና በፍትሃዊነትስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤ የምርምር ግብዓቶችን የመለየት፣ የማቅረብ፣ የማከፋፈል፣ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ መዋላቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 2. የእቅዱ መነሻና ታሳቢዎች

### የእቅዱ መነሻ

የምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት በ2007 ዓ.ም አቅዶ ከፈጸማቸውና ታቅደው ሳይፈጸሙ በቀሩ እንዲሁም ሳይታቀዱ በተከናወኑ ቁልፍ ተግባራት ላይ ተመርኩዞ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን እንዲሁም ተግዳሮቶችን አጢኖ በመፈተሽ  እና የዩኒቨርሲቲው የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በመመስረት ይህን የ 2008 ዓ.ም የስራ እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ ይህ እቅድ ሲዘጋጅ እንደውስጣዊ ሁኔታዎች ሁሉ የውጫዊ ሁኔታዎችን ተጢነው ነው፡፡ በተለይም ከቅርብ ገዜ ወዲህ የምርምር እና የቴክኖሎጂ ስርጭት ለሀገሪቱ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት የሚጫወተውን ሚና በመገንዘብ መንግስት ለዚህ ዓላማ ለዩኒቨርሲው የሚመድበው ገንዘብ እየጨመረ በመምጣቱ  ጽ/ቤቱ ይህን በመገንዘብ ችግር ፈቺ ምርምሮችንና የቴክኖሎጅ ስርጭቶችን በማስፋት የጎላ አስተዋጽኦ ለማበርከት ይህንን ዓመታዊ የስራ እቅድ አዘጋጅቷል፡፡

### የእቅዱ ታሳቢዎች

እቅዱን ለማሳካት የሚከተሉት ውስጣዊና ውጫዊ ታሳቢዎች ከግንዛቤ ገብተዋል

**ውስጣዊ**

1. ዩኒቨርሲቲው በአዲስ መልክ ላወጣቸው የምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች ስር ለሚገኙት ንዑስ የምርምር ትኩረት መስኮች አስተባባሪዎች ይመደባሉ፡፡

2. የዩኒቨርሲቲው ICT አገልግሎት ደንበኛን ያማከለ፤ የተሳለጠና አስተማማኝ ይሆናል፡፡

3.የዩኒቨርሲቲው የግዥ ስርአት ፈጣን፤ ጥራቱን የጠበቀና የተሳለጠ ይሆናል፡፡

4. የፋይናንስ ስርዓቱ ደንበኛን ያማከለ፤ ፈጣን እና የተሳለጠ ይሆናል፡፡

5. ተመራማሪዎች፤ ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎች የምርምርና የቴክኖሎጂ ስርጭት ስራን በመደገፍ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ፡፡

6. ዩኒቨርሲቲው ለተማራማሪዎች በቂ የመጓጓዣ መኪናዎችን ይመድባል፡፡

**ውጫዊ**

1. የባልድርሻ አካላት በተለይም የወረዳና የዞን ቢሮዎች እና የከተማ አስተዳደር አካላት ባጠቃላይ ማህበረሰቡ በምርምርና ስርጸት ስራው ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡
2. ለግብርና ምርምርና ስርጸት ወቅቱን የጠበቀ በቂ ዝናብና ሌሎች ተጓዳኝ ምቹ የምርት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡
3. በጀትን ያመጣጠነ በቂ የጉልበት ሰራተኛ በወቅቱ ይገኛል፡፡

## 3. የምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴትና መሪ ቃል

### ተልዕኮ

ፍላጉት-ተኮርና ጠቃሚ ምርምሮችን በተለያዩ መስኮች በማካሄድ የምርምር ቴክኖሎጂዎችን፣ እውቀቶችንና መልካም ተመክሮዎችን በማፍለቅ፣ በመለየትና በማሰራጨት የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻልና ማሳደግ፡፡

### ራዕይ

የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ በ2025 G.C ከአፍሪካ በምርምር ተመራጭ ከሆኑ ጥቂት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ እንዲሆን ማስቻል፡፡

### እሴት

1. **አካዳሚያዊ ነፃነት፡-**የመማር-ማስተማርና የምርምር ስራዎች በነጻነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲካሄዱ፣ ግለሰቦች ጥልቅ ምርምር ማድረግ እንዲችሉ፣ በመማር-ማስተማር፣ በምርምርና በልማት ስራዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ዩኒቨርሲቲው በቁረጠኝነት ይሰራል፡፡
2. **ቁርጠኝነት፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተሰጣቸውን ስራና የተጣለባቸውን ሀላፊነት ዕውቀታቸው በፈቀደ ደረጃ በቁርጠኝነት፣ በተነሳሽነትና በታማኝነት ለመወጣት የሰራሉ፡፡
3. **መልካም አስተዳደር፡-**ዩኒቨርሲቲው ዴሞኪራሲያዊ፤ ግልፅ፤ ሁሉን አሳታፊ፤ ሀላፊነትና ተጠያቂነት የተመላበት አመራርን ያሰፍናል፤የእኩል ተጠቃሚነት መርሆን ያራምዳል፡፡
4. **ልዩነትን ማክበር፡-**ዩኒቨርሲቲው እኩልነትና ፍትሀዊነት በሁሉም መልኩ እንዲሰፍን ልዩነቶችን (በፆታ፤ በብሄር፤በሀይማኖት፤በዘር፣ በጎሳ፤ በእድሜ፤ በአካል ሁኔታ፤ ወዘተ..) አክብሮ ይሰራል፡፡
5. **ሙያዊ አሰራርን መሰረት ማድረግ፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለላቀ ሁሉን ዓቀፍ ሙያዊ ስነምግባር ተገዥ ይሆናል፡፡
6. **በጋራ የመስራት ባህልንማዳበር፡-**የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እርስ በርስና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመግባባት በጋራ የመስራት ባህልን ያዳብራሉ፤ የእኛነትን መንፈስና ሃላፊነትን የመቀበል መርሆ ያሳድጋሉ፡፡
7. **የፈጠራ/ግኝት ክህሎትን ማዳበር፡-**የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብየስራ፣ የአዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች ባለቤት የመሆንና አቀናጅቶ የመተግበር ባህልን ያዳብራል፡፡
8. **ተፈጥሮና አካባቢን መንከባከብ፡-**ዩኒቨርሲቲው የተፈጥሮ ሀብትንና አከባቢን ለመጠበቅ፣ለመንከባከብና፣ በአግባቡና ተፈጠሮን በማይጎዳ መልኩ ለመጠቀም በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡

**መሪ ቃል፡** ለልማት መሰረት እንጥላለን!

### 4. ከዩኒቨርሲቲው ወደ ምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤትና ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈጸሙ ዋናዋና ተግባራት በትኩረት መስክ

# የትኩረት መስክ2፡ በምርምር መላቅ

## i) የዝግጅት ምእራፍ ስራዎች

- ከተለያዩ ኮሌጆች ለተውጣጡ መምህራን የንድፈ ሀሳብ አጻጻፍና የመረጃ ትንተና እንዲሁም የሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት
- በባለድርሻ አካላትና በደንበኞች የምርምር ፋሲሊቲ አጠቃቀምና አቅርቦት ዙሪያ ዳሰሳ ማካሄድ
- የምርምር ቡድኖችን ማቋቋም እና የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎችን መለየት
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለተውጣጡ ሞያተኞች በምርምርና ቴክኖሎጅ ሽግግር ክህሎት ስለጠና መስጠት
- በዩኒቨርሲቲው የገንዘብድጋፍ በመካሄድላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን በማከናወን ማጠናቀቅ

## ii) የትግበራ ምእራፍ ስራዎች

**ግብ 1፡ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና እርካታ ማሳደግ**

ውጤት፡ *ያደገ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና እርካታ*

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. ዓመታዊ የገበሬዎች እና ሌሎች የልማት አጋሮች የመስክ ቀን ማካሔ፡ ባለፉት ሩብ አመታት ግን ዓመታዊ የገበሬዎች እና ሌሎች የልማት አጋሮች የመስክ ቀን ለማካሔድ በታቀደው መሰረት በዋናው ግቢ፣ በኮምቦልቻ፣ በግራዋ፣ በባቢሌ እና በፌዲስ ወረዳዎች የተለያዩ የልማት አጋሮች በተገኙበት በአሉ የተካሄደ ሲሆን፣ ይህም ተጨባጭ የምርምር እና ስርጸት፣ የመልካም ተሞክሮ ማስፋፋት ውጤቶችን በአርሶ አደሮችና ተመራማሪዎችን ጨምሮ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመስክ ላይ በመገኘት ለማየትና ለመገምገም ተችሏል፡፡




በአራተኛው ሩብ አመት የድሪፕ እና ስፕሪንክለር ቴክኖሎጂን ለማስተዋወቅ በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ መጀመሪያ ቴክኖሎጂውን በማስመረቅና የአሰራር ሂደቱን ለማሳየት የሚመለከታቸው ባለሙያዎችና የመንግስት ሀላፊዎችና አርሶ አደሮች እንዲሁም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ የተሳተፈባቸው የመስክ ጉብኝቶች ተከናውኖአል፡፡ እንዲሁም የዚህ ቴክኖሎጂ ውጤት ጥቅም ላይ ከዋለ በኃዋላ የተገኘውን መልካም ተሞክሮ ለማካፈል አርሶ አደሮችና የዩኒቨርስቲው አመራር የተሳተፉበት የመስክ ቀን ተካሂዶአል፡፡














2. የደንበኞችና የባለድርሻ አካላት የቴክኖሎጂ ፍላጎት ዳሰሳ በተለያዩ ወረዳዎች ላይ ለማካሄድ በታቀደው መሰረት 12 የምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ወረዳዎች ተዳሰው 40 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት ተለይተው በቀጣይ በቴክኖሎጂ ተደራሽ ለማድረግ የዝግጅት ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡
3. በማህበር የተደራጁ ሴቶችን የተክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በተየዘው እቅድ መሰረት፤ በሚታ አብዲ ቦሩ የሴቶች ማህበር፤ቢሲዲሞ ሌሊሴ የሴቶች ማህበርን ተጠቃሚ ለማድረግ የቦቆሎና ስንዴ ምርጥ ዘር እንዲያመርቱ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በአራተኛው ሩብ አመትም ይህው ስራ ተጠናክሮ ቀጥሎአል፡፡





4. የሴቶችን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማጎልበት፡ በምርምር እና ስርጸት ስራዎች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የሚከናወኑ ማናቸውም ስራዎች የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማጎልበት በሚደረገው ጥረት፤ ከማንኛውም የምርምር እና ስርጸት ስራ ከተሳታፊው ቢያንስ 10 ፐርሰንቱ ሴቶች እንዲሆኑ በተያዘው ግብ መሰረት፤ የምርጥ ዘር ስርጭት፤ በመስክ ቀን ጉብኝትና ውይይት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ የሴቶችን ተሳታፊነት ከፍ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ፤ በስልጠና፤ አቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ተሳታፊነታቸውን ከፍ ለማደረግ ተጥሮአል፡፡



**ግብ 2፡ የምርምር አጋርነትንና ትስስርን ማሳደግ**

ውጤት፡ ያደገ አጋርነትና ትስስር

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. ምርምር የሚሹ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመለየት እና ንድፈ ሐሳብ ለመቅረጽ በተያዘው እቅድ መሰረት የሐይል፤ ምህንድስናና የመረጃ ቴክኖሎጂ የምርምር ትኩረት አቅጣጫ መሪ ከቡድኖቹ

ጋር በመሆንነ በሐረር ቢራ እና በአዳማ የእርሻ መሳሪያዎች ኢንደስትሪ የዳሰሳ ምልከታ እና ውይይት ያደረገ ሲሆን በጥሩ የመግባባትና የመረዳዳት መንፈስ አብሮ ለመስራት ተስማምተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዚሁ ትኩረት አቅጣጫ መሪ፣ ከዩኒቨርስቲው የቴኬኖሎጂ መምህራንና የዩኒቨርስቲው የማህበረሰብ ተኮር ትምህርት ጋር በመሆን የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን ባዘጋጀው የባለድርሻ አካላት ስብሰባ ላይ በመገኘት፣ ገንቢ ውይይት አድርጎአል፡፡ በዚህም ሐረማያ ዩኒርስቲ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጋር እንዴት ምርምሮችን አቀናጅተው እንደሚሰሩ ተመካክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከኢንደስትሪዎች ጋር የምርምር ትብብር መፍጠር የመግባቢያ ሰነድ የተፈረመ ሲሆን፣ የጋራ ንድፈ ሀሳብ ለመቅረጽ በዝግጅት ላይ ነው፡፡

2. ነባር ዘር አምራች ማህበራትን ዘር በጥራት ያመርቱ ዘንድ መከታተልና መደገፍ፣ ዩኒቨርስቲው እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ፣ 42 ነባር ምርጥ ዘር አምራች ማህበራትን በምስራቅና ምእራብ ሀረርጌ፣ በተቀናጀ የምርጥ ዘር ፕሮግራም ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን ማህበራቱም ዘር እያመረቱ ለአርሶ አደሮች እያቀረቡ ሲሆን፣ የምርጥ ዘር እጥረትን በመቀነስ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡



የዘር አምራች ማህበራትን ለማጠናከር የተሰጠ ስልጠና በከፊል

3. 33ኛ አመታዊ የምርምር እና ስርፀት ጉባኤ በስድስቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ለማካሔድ በተያዘው እቅድ መሰረት በዘንድሮው አመት ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ የዩኒቨርስቲው የምርምር ስርጸት ጉባኤ ተካሂደዋል፡፡ ይህ ዝግጅት ለሶስት ቀናት የተካሄደ ሲሆን የመጀመሪያው ቀን የማህበረሰቡ እና የባለድርሻ አካላት ቀን ተብሎ የተከበረ ሲሆን በዚሁ ቀን ውይይቱ በአካባባው ማህበረሰብ ቋንቋ (በዋናነት በአፋን ኦሮሞ) የተካሄደና ከዚሁ ጎን ለጎን የዩኒቨርስቲውን የምርምር ስራ የሚስተዋዉቅ አውደ ርእይ ተካሂዶአል፡፡ በዚህ ዝግጅት ላይም 350 ተሳተፊዎች ታድመዋል፡፡

ሁለተኛውና ሶስተኛው ቀን ደግሞ 86 የጥናት ውጤቶች ለ123 ተመራማሪዎችና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ቀርበዋል፡፡





33ኛ አመታዊ የምርምር እና ስርፀት ጉባኤ በከፊል

4. ለ2009ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሳቦችን ለውድድር ለመጋበዝ በታቀደው መሰረት በዚህ ሩብ አመት ጥሪው ተከናውኖ 270 ያህል የምርምር ንድፈ ሀሳቦች የገቡ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ተካሂዶ፤ ለሁለተኛው ዙር ግምገማ በዝግጅት ላይ ነው፡፡
5. በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮረ ኮንፈረንሶችን ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት፤ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ ሁለት ታላላቅ ኮንፈረንሶችን አዘጋጅቶል፡፡ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ ኢንዴፕዝ ከሚባል አለም አቀፍ ድርጅት እና ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ አምስት የጤና እና ዴሞግራፊክ ክትትል ምርምር ማእከላት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ የተካሄደ ሲሆን፤ በዚህ ኮንፈረንስ በቀርሳ ዴሞግርፊክና ጤና ምርምር ማእከል የተሰሩ ስድስት የምርምር ስራዎች ቀርበዋል፡፡ በዚህ ሳይንሳዊ በአጠቃላይ ከ350 ያለነሱ አለም አቀፍ ሳይንቲስቶች የተሳተፉ ሲሆን በአራት የጎንዮሽ ስብሰባዎች ከ150 በላይ የምርምር ጽሁፎች ቀርበዋል፡፡ ይህንን ስብሰባ የጤና ጥበቃ ሚንስትር ዴኤታ በንግብር የከፈቱት ሲኖን የተከበሩ ዶ/ር ከሰተብርሀን አድማሱ ማጠቃለያ ሰጥተውበታል፡፡




በዚህ አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ የዩኒቨርስቲው ፕሬዚሀዳንት ፕ/ር ጨመዳ ፊኒንሳ፣ እና ፕ/ር ንጉሴ ደቻሳ የተሳተሳተፉ ሲሆን፣ ፕ/ር ጨመዳ ንግግር ሲያደርጉና ተሳታፊዎች በከፊል፡፡

በዚሁ ሩብ አመት ዞዋ ከሚባል አለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በመተባበር በእርጥበት አጠር ቦታዎች ለአደጋ ተጋለጭነት መቀነስ እና ምርታማነትን ማሳደግ በሚል አገር አቀፍ ሳይንሳዊ ስብሰባ በዚሁ በዋናው ግቢ የተካሄደ ሲሆን 22 የሚሆኑ ምርምር ጽሁፎች በ4 ዋና ዋና መሰረታዊ ሀሳቦች ላይ ተካሂደዋል፡፡ በዚህም 120 ተመራማሪዎች ከተላያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት፣ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በሶስተኛው ሩብ አመት ISSD ፕሮጀክት፣ አለም አቀፍ የምክክር ጉባኤ በድሬ ዳዋ የተካሄደ ሲሆን፣ አላማውም ጥራት ያለው ዘር በሚመረበትና በሚጠበቅበት ሂደት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የስታትሲትክስ ትምህርት ክፍል የስታትስቲክስን አጠቃቀም በግብርና ምርምር በሚል አለማቀፍ ኮንፈረንስ ያካሄደ ሲሆን 150 ያህል ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፡፡በዚህም ስብሰባ ላይ 20 ያህል የምርምር ጽሁፎች የቀረቡ ሲሆን፣ ሳይንሳዊ ትንተናም ተሰጥቶባቸዋል፡፡




የስታትስቲክስ ለግብርና ምርምር ኮንፍረንስ ላይ ተሳታፊዎቸ በከፊል

ከዚህ በተጨማሪ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን ያከናወነው አቤት ተግባር አንዱ፣ አለም አቀፍ የተቢ ቀንን አስመልክቶ ሁሉን እንድደረስ፣ በተቢ መሞት ይብቃ በሚል አርስት ለአራት ተከታታይ

ቀናት በደሬዳዋ ሲካሄድ የቆየውን የቲቢ ኮንፈረንስ ማዘጋጀቱ ነው፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ፤ በአለም ጤና ድርጅት ተወካዮች የተገኙ ሲሆን፤ በአገሪቱ አሉ የተባሉ የቲቢ ተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን በፖስተርና በቃል አቅርበዋል፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ከ 38 በላይ ጽሑፎች የቀረቡ ሲሆን 350 በላይ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፡፡ የዚህ ስብሰባ ማጠናቀቂያ በሐረማያ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተከናወነ ሲሆን፤ በመዝግያው ፕሮግራም ላይ አትሌት ደራርቱ ቱሉ፤ የቲቢ መከላከል አምባሳደር በመገኘት መዝጊያውን አድምቃዋለች፡፡






የመዝግያ ፕሮግራሙን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች

በአራተኛው ሩብ አመት የግመል የወተትና የወተት ተዋጽኦ ቴክኖሎጂዎች ላይ ያተኮረ ኮንፍረንስ የተካሄደ ሲሆን የምርምር ቢሮው በዚህ ስራ ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጎአል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተፈጥሮ እና ቀመር ኮሌጅ ባዘጋጀው ኮንፍረንስ ላይ ድጋፍ አድርጎአል፡፡

## ግብ 3፡ **ፍላጎት ተኮር የምርምር ውጤቶችን ማሳደግ**

ውጤት፡ የጨመረ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅና ለማላመድ በተያዘው እቅድ መሰረት 30 የእንስሳትና እጽዋት የተሻሻሉ ዝርያዎችን በተለያዩ የዩኒቨርስቲው ምርምር ጣቢያዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት የማስተዋወቅና የማላማድ ስራ እየተሰራ ነው፡፡



በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ የተለያዩ የሰብል ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ በተደረገው ጥረት ስድስት የማሽላ፣ ሰባት የበቆሎ፣ አራት የስንዴ፣ ሁለት የቦሎቄ፣አንድ የአተር፣ አንድ የባቄላ፣ ሁለት የሽንብራ፣ ሁለት የድንች፣ አንድ የነጭ ሽንኩርት፣ አንድ የካሮት፣ ሶስት የከብት መኖ ፡ ሁለት የሰሊጥ፣ አንድ የጤፍ፣ ሶስት የለውዝ ዝርያዎች በሐረማያ፣ በደደር፣ በፌዲስ፣ በባቢሌ፣ በጭናክሰን፣ በጎሮ ጉቱ፣ በሜታ፣ በሂርና፣ በግራዋ፣ በኩረፋ ጨሎ፣ በቀርሳ፣ በጉርሱም፣ በኮምቦልቻ እና በጃርሶ ወረዳዎች 40 የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላትን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኖ ዘር በመዘራት ላይ ነው፡፡



2. የዘር ብዜት ስራ፡ የድንች፣የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የማሽላ፣ የካሮት፣ የነጭ ሽንኩርት፣ የስኳር ድንች እና ምርጥ ዘሮችን ለማባዛት በተያዘው እቅድ መሰረት 16 ሄክታር መሬት ላይ በዩኒቨርስቲው በሚገኘው የምርምር ጣቢያዎች፣ የምርጥ ዘር ብዜት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥራቱ የተመሰከረለት ዘር ለማምረት በተያዘው እቅድ መሰረት 497.5 ኩንታል የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የድንች፣ ሰብል ዘሮችን ለማምረት ተችሎአል፡፡ በሶስተኛ ሩብ አመት በተጨማሪ 35 ሄክታር የድንች ዘር ብዜት ተከናውኗል፡፡





የድንችና የስንዴ ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት የተነሳ ፎቶ

በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ በ13 ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ ዘሮችን በዩኒቨርሰቲው የተለያዩ የምርምር ጣቢያዎች በመባዛት ላይ ይገኛሉ፡፡

3. ጥራቱ የተመሰከረለት ዘር  እንዲመረት ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት የዩኒቨርስቲው ከፍተኛ ባለሙያዎች በተለየያዩ አምራች ማህበራት ያመረቱትን ዘር የጥራት ደረጃ በመከታተል እና በመገምገም ከ640 ኩንታል በላይ ጥራቱ የተመሰከረለትን ዘር የሽያጭ ፍቃድ ሰጥተዋል፡፡
4. የተሸሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ማባዛት፤ በቢፍቱ ገዳ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት 40 የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ተባዝተዋል፡፡
5. የተሸሻሉ ፍየልና በግ ዝርያዎችን ለማባዛት በተያዘው እቅድ መሰረት ባለፉት ሩብ አመታት 150 የስጋ ምርታቸው ከፍተኛ የሆነ፤ በሽታን የመቋቋም ችሎታቸው ከፍተኛ የሆነ፤ ለየአየር ንብረቱ ተስማሚ የሆኑ የተሻሻሉ የፍየል ዝርየዎች ተባዝተው ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ተዘጋጅቷል፡፡ በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ 50 ፍየሎች ተባዝተው ለአካባቢው ማህበረሰብ ተከፋፍለዋል፡፡



6. የተሸሻሉ የስጋ ከብት ዝርያዎችን ለማባዛት በተያዘው እቅድ መሰረት ባለፉት ሩብ አመታት 8 የስጋ ምርታቸው ከፍተኛ የሆነ፤ በሽታን የመቋቋም ችሎታቸው ከፍተኛ የሆነ፤ ለየአየር ንብረቱ ተስማሚ የሆኑ የተሻሻሉ የፍየል ዝርየዎች ተባዝተው ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ ሩብ አመት ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ 5 የስጋ ከብቶች መለየት ተችሎአል፡፡

7. በዩኒቨርስቲው የበጀት ድጋፍ በስድቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫ የሚካሄዱ 348 ምርምሮችን ለመከታተልና ለመደገፍ በተያዘው እቅድ መሰረት በስድስቱም የምርምር የትኩረት መስኮች አስፈላጊው የድጋፍና ክትትል ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን፤ ተመራማሪዎች ስራቸውን በመልካም ሁኔታ እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡
8. በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት ድጋፍ የሚካሄዱ 113 ምርምሮችን ለመከታተልና ለመደገፍ በተያዘው እቅድ መሰረት በተለይ በአዝእርትና እና እንስሳት ምርምር መስኮች የምርመር ስራዎች በተጠናከረ መልኩ እየተከናወኑ ሲሆን አስፈላጊው ፋሲሊቲዎችን የማመቻቸትና ለምርምሩ የሚያስፈልጉ ድጋፎች ለተመራማሪዎች እየተደረገ ይገኛል፡፡
9. በስድስቱ የምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች ከሚካሄዱት የምርምር ስራዎች ውስጥ 66ቱ ተጠናቀዋል፡፡

## ግብ 4፡ የምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና ህትመት ማሻሻል

*ውጤት፡ የተሻሻለ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሽራዎችና የምርምር የህትመት ውጤቶች*

*ዋና ዋና ተግባራት፡*

1. ባለፉት ሶስት ሩብ አመታት ሁለት መቶ የድንች ዘርና 620 የተለያዩ የበቆሎ ዝርያዎች በድምሩ 820 ኩንታል ዘር ስርጭት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም 420000 የስኳር ድንች ቁርጥራጭ በገንዘብ ሲተመን 212500 ብር የሚሆን በደርቅ ለተጎዱ ወገኖች ለምስራቅ ሀረርጌ (ለፈዲስ ወረዳ 50000 ለሐረማያ 325000) እና ምእራብ ሐረርጌ 50000 ቁርጥራጭ ተሰራጭቷል፡፡
   የተለያዩ ዘሮችን ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት በታቀደው መሰረት፤ በጎረ ጉቱ፤ በፈዲስ፤ በሜታ፤ በጭናቅሰን፤ በሀረማያ፤ በጃርሶ እና ጉባ ቆርቻ ወረዳዎች 50 ኩንታል የተለያዩ የስንዴ እና የሽንብራ የቦቆሎ እና የቦሌቄ ምርጥ ዘሮችን ለምስራቅና ምእራብ ሀረርጌ አርሶ አደሮች በማሰራጨት የምርጥ ዘር ተጠቃሚ በመሆን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡



የድንች ዝርያዎችን ለአርሶ አደሮች ለመስጠት በዝግጅት ላይ

   በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ 500 ኩንታትል የተለያዩ የድንች፤ የቦሎቄ፤ የስንዴ፤ የማሽላ፤ እንዲሁም 250 ሺ ቁርጥራጭ የስኳር ድንች ቁርጥራጭ በድርቅ ለተጎዱ የመስራቅ እና ምእራብ ሐረርጌ ወረዳዎች፤ ለሱማሌ ክልል ተሰራጭቶአል፡፡

2. በሶስተኛው ሩብ አመት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት 50ኛ አመቱን ሲያከብር ባዘጋጀው ኤግዚብሽን፤ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ፤ እስከ ዛሬ ድረስ በምርምር የወጡትን ዝርያዎች ያስተዋወቀ ሲሆን ዝግጅቱንም የመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች ጎብኝተውታል፡፡







የመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች የሐረማያ ዩኒቨርሰቲን ቡዝ በጎበኙበት ወቅት

በአራተኛው ሩብ አመት ዩኒቨርስቲው በሶስት ኩነቶች ላይ አውደ ርእይ ያቀረበ ሲሆን፤ እነዚህም በአዲስ አበባ በተካሄደው የሀያ አምስተኛው የግንቦት ሀያ በአል፤ ዩኒቨርስቲው ባካሄደው 33ኛው የምርምርና ስርጸት በአል፤ እንዲሁም የ2008 የተማሪዎች ምረቃ በአልን አስመልክቶ በተካሄደው አውደ ርእይ ላይ በርከት ያሉ የምርምር ስራ ውጤቶች፤ መልካም ተሞክሮዎች ቀርበዋል፡፡








የአውደ ርእይ ላይ ተሳትፎ በከፊል

3. የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላትን በቴክኖሎጂ ለመድረስ በተያዘው እቅድ መሰረት በአርባ ማእከላት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች በሰርቶ ማሳያ ቀርበዋል፡፡
4. በሶስተኛው ሩብ አመት ከዞዋ አለም አቀፍ ድርጅት ጋር በመተባበር በሚደጋ ቶላ ለሚገኙ አርሶ አደሮች 500 ያህል የተሻሻሉ የዶሮ ቦቶችን በዩኒቨርስቲው ተሰርተው እንዲሰራጩ ተደርጎአል፡፡



የዶሮ ቤት ምርት ለማሰራጨት በስራ ላይ

በትግበራ ላይ ያሉ ቴክኖሎጂዎቸዎችን በሁለተኛው ሩብ አመት ለተጠቃሚዎች ለማስታዋወቅ በተየዘው እቅድ መሰረት፣ በሐረር ከተማ በተዘጋጀው አገር አቀፍ ኤግዚቢሽን ላይ ዩኒቨርስቲው የተሳተፈ ሲሆን የዶሮቤት ቴክኖሎጂ፣ የተለያዩ አይነት የሰብልና አትክልት የተሸሻሉ ዘሮችን ለማህበረሰቡ አስተዋውቆአል፡፡

5. የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ለመድረስ ታቅዶ በመጀመሪያው ሩብ አመት 30 የተለያዩ የስንዴ፣ የቦቆሎ፣ የለውዝ፣ የሰሊጥ፣ የድንች፣ የማሽላ፣ የሽምብራ፣ የቦሎቄ እና እንስሳት ቴክኖሎጂዎች በ21 የአርሶ አደር የስልጠና ማእከላት ላይ የሰርቶ ማሳያ ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡
6. ለወረዳ ሙያተኞች የልማት ሰራተኞች፣ ለአርሶ አደሮችና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የተለያዩ ክህሎት ማዳበሪያ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በአጠቃለይ በሶስቱ ሩብ አመት 650 ሰልጣኞች በተለያዩ ሙያ የማብቃት ስልጠናዎች አግኝተዋል፡፡





በለውዝና የተለያዩ ሰብሎች ስልጠና ሲሰጥ በከፊል የሚያሳይ ፎቶ

7. በአመቱ 32ኛው የምርምር ጉባኤ በጽሁፍ መልክ በሶስት ጥራዝ ታትሞ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን ለተጠቃሚም ተከፋፍሎአል፡፡ በተጨማሪም ከዚዋ ጋር በተደረገው ስምምነት፤ በተካሄደው "Building resilence and reducing vulnerability in moisture stress areas through climate smart technologies and innovative practices" በሚል ርእስ የተካሄደው የወርክ ሾፕ ፕሮሲዲንግ ታትሞ ተሰራጭቶአል፡፡
8. የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር መጣጥፎችን (articles) በታዋቂ ጆርናሎች ላይ በአመቱ 10 እንዲታተሙ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በዘጠኝ ወሩ በድምሩ ዘጠኝ መጣጥፍ ላማሳተም የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
9. የዩኒቨርሲቲውን ጆርናሎች የተለያዩ ቮልዩሞችና እትሞች ማሳተም በተያዘው እቅድ ሁለት ታትሞ የወጣ ሲሆን አራቱም ቮሊዩም በድረ ገጽ ተለቋል፡፡
10. በአመቱ ለማሳተም ከተያዙት የምርምር ፓሊሲ እና መመሪያ ሰነዶች ውስጥ የህትመት መመሪያ ታትሞ ተሰራጭቶአል፡፡
11. የምርምር ሥራዎች እና የምርምር ውጤቶችን የሚያስተዋውቁ በራሪ ጽሁፎችን፤ ፖስተሮችን ባነሮችን፤ መጽሂቶችን፤ ሚኒ ሚዲያዎችን እንዲሁም የሬዲዮና የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ማሰራጨት በተየዘው እቅድ መሰረት፤ ዜናዎች እና አዳዲስ ቴክኖሎዎችን በቴለቪዥን እና በሬዲዮ በተለያዩ ግዜአት የተላለፉ ሲሆን በሳምንት አንድ ግዜ ደግሞ በግቢው የማህበረሰብ ሬዲዩ (ኤፍ ኤም 91.5) በመጠቀም የምርምር ግኝቶችን ለአድማጭ በማስተላለፍ ላይ ነው፡፡

   የ33ኛ የምርምር ጉባኤን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀው ልዩ የምርምር መጽሄት ለአንባቢ በበአሉ ላይ የተሰራጨ ሲሆን፡ በአመቱ የምረቃ በአል ላይም እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

12. በፊት ከነበረው EAJS በተጨማሪ ሶስት አዳዲስ ጆርናሎች የዝግጅት ስራ ተጠናቆ የህትመት ስራ ሂደት የተጀመረ ሲሆን በቅርብ ስራቸውን አጠናቀው የመጀመሪያ ህተመታቸውን የአንባባቢ ያስራጫሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የህግ ሪቪው በሚል የሚታወቀው ህትመት፡ የጥራት ደረጃውን አሻሽሎ ወደ ጆርናል ደረጃ እንዲያድግ ጥረት ተደርጎ በዚሁ መሰረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

## ግብ 5፡ የምርምር ድጋፍ ምንጮችን (research funds) ማሳደግ

ውጤት፡ ያደገ የምርምር ድጋፍ ምንጮች

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. የምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶችን የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ለማስቻል በተየዘው እቅድ መሰረት ከብርቱካን፣ ከስኳር ድንች ቁርጥራጭ፣ ከሎሚ፣ ከዶሮ ቤት ቴክኖሎጂ ከፍየል እና ከበግ፣ ከቲማቲም፣ ከጎመን፣ እና ከመሳሰሉት የምርምር ተረፈ ምርቶች 2.55 ሚሊየን ብር ተገኝቶአል፡፡
2. ከግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት ጋር በመተባባር ለሚደረገው ምርምር በአመቱ 1.2 ሚሊዩን ብር ተገኝቷል፡፡
3. ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር የምርምር ድጋፍ ማግኘት በተየዘው እቅድ መሰረት በዚህ አመትም ከተለያዩ የምርምር ድጋፍ አካላት ለማግኘት በተደረገው ጥረት በዚህ ሩብ አመት ከ ZOA፣ HCS; ከድሬ ዳዋ ግብርና ቢሮ፣ እና ሌሎችም በድምሩ 2.05 ሚሊየን ብር የተገኘ ሲሆን በጠቅላላው በአመቱ 14.05 ሚሊየን ብር ለምርምር ስራ በግብርና፣ በጤና፣ በህግ እና ሌሎችም የምርምር መስኮች ድጋፎች ማግኘት ተችሎአል፡፡

## ግብ 6፡ የሐብት አጠቃቀምን ስልጠት ማሳደግ

ውጤት፡ የተሳለጠ የሀብት አጠቃቀም

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. የምርምር ፈንዶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን በምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት፣ ተመራማሪዎች በሩብ አመቱ በያዙት እቅድ መረት ለሰሩት ስራ ሪፓርት ያስገቡ ሲሆን ሪፓርቱም በምርምር ትኩረት አቅጣጫ መሪዎች ተገምግሟል፡፡
2. የመስክ ጉብኝትና ክትትል፣ ሶስቱም ዳይሬክተሮች እና በተዋረድ ባሉ ባለሙያዎች በተመራማሪዎች እና መስክ ሰራተኞች በተገኙበት በሩብ አመቱ ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎች በትክክል ለመሰራታቸው የመስክ ላይ ምልከታ የተደረገ ሲሆን፣ የገጠሙዋቸው ችግሮች ለመፍታት ተሞክሮአል፡፡

## ግብ 7፡ የስራ ሂደቶችን ቅልጥፍናና ስልጠት

ውጤት፡ የተቀላጠፈና የተሳለጠ የስራ ሂደቶች

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. የመወሰን ዓቅምን ማሳደግና ያልተማከለ አሰራርን ለማስፈን በተያዘው እቅድ መሰረት አንድ የጋራ ውይይት በምርምር ምክትል ፕሬዚደንት ደረጃ ከዳይሬክቶሮች እና የምርምር ትኩረት መሪዎች ጋር የተደረገ ሲሆን፤ ስራን በአግባቡ እና በፍጥነት የሚሰራበትን እና ውጤታማ የምርምር ሂደት የሚሰፍንበትን የስራ አቅጣጫ ተሰጥቶአል፡፡
2. የምርምር ትኩረት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የንኡስ ምርምር ትኩረት አቅጣጫዎችን መስኮችን ማዋቀርና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተያዘው እቅድ መሰረት በ21 የንኡስ የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ተመራማሪዎች የተዋቁረ ሲሆን ለሚቀጥለው የበጀት አመት ምን ምን ስራዎች በዋናነት በስራቸው ሊሰሩ እንደሚገባቸው እየተወያዩ እና በምርምር ንኡስ አቅጣጫ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነገሮች በመንደፍ ላይ ናቸው፡፡
3. የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፤ የአመቱ ስራ ከመጀመሩ በፊት በተለያዩ የምርምር ማእከላት ለሚሰሩ ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠና ተሰጥቶአል፡፡ በተጨማሪም በስራ ላይ ያሉ ሀላፊዎችን በስራ ሂደት ላይ ስላጋጠሙ ችግሮችና አፈጻጸም ክፍተቶች ውይይት ተደርጎባቸው የተሻለ የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ተችሎአል፡፡
4. መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የልማት ሰራዊት መገንባትና መከታተል፤ የስራን ቀልጣፋና የተሳለጠ ለማድረግና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን 20 የልማት ሰራዊት ተገንብቶ በምርምር ማእከላት ስራን በተቀላጠፈና በተደራጀ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## ግብ 8፡ የአመራር ብቃትንና ተነሳሽነትን ማሳደግ

1. የአመራር ብቃትን ላማሳደግ ለ17 የምርምር ጣቢያ አስተባባሪዎችና የመስክ ተቆጣጣሪዎች ሰራተኛን ማብቃት (personel development)፤ ሰራተኛን የስራ አገማገም ስርአት (staff appraisal)፤ በቡድን መሰራት (team work)፤ ለስራ ተነሳሽነትን ማበረታታት (motivation)፤ እንዲሁም የሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ደንብና መመሪያዎች ላይ ለሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቶአል፡፡
2. የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት፤ በጀርመን፤ በታንዛንያ፤ በኡጋንዳ፤ በጋና እና በአሜሪካ ምርምር ላይ የሚሰሩ መምህራን ጉብኝት ያደረጉ ሲሆን በጉብኝቱም ጠቃሚ ልምድ ተገኝቶአል፡፡ እንዲሁም በአገር ውስጥ በሚገኙ ታዋቂ የምርምር እና የትምህርት ተቋማት የስራ ጉብኝት የተደረገ ሲሆን ጠቃሚ ልምድ ተገኝቶአል፡፡
3. በአመቱ 65 ለሚሆኑ ለምርምር ቴክኒክና የመስክ ረዳቶች በመረጃ አያየዝና አጠነቃቀር ላይ ስልጠና ተሰጥቶአል፡፡
4. ለመምህራን የምርምር ንድፈ ሃሳብ፤ የመረጃ አያያዝና ትንተና ስልት፤ ሳይንሳዊ መጣጥፍ አዘገጃጀትና የውጤት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት በተያዘው እቅድ መሰረት ለመምህራን የምርምር  የንድፈ ሃሣብ አዘገጃጀትና የሳይንሳዊ መጣጥፍ (Paper) አዘገጃጀትና የውጤት አቀራረብ ላይ ስልጠና ለመስጠት በተያያዘው እቅድ  መሰረት ከተለያዩ ኮሌጆች ለተውጣጡ መምህራን SPSS የስታስቲክ ሶፍትዌር እና የንድፈ ሃሣብ የሳይንሳዊ መጣጥፍ (Paper) አዘገጃጀት ስልጠና በአማካኝ ከ 103 ሠልጣኞች በተሳተፉበት በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሚሰሩ ባለሞያዎች ስልጠናው ተሰጥቶል፡፡
   SPSS በመሰረታዊ ሳይንስ፤ በማህበረሰብና ሀብረተሰብ፤ በበኢነርጂ& ኢንጂነሪንግና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የምርምር የተኩርት መስክ ለሚመራመሩ መምህራን በሚጠቅም መልኩ  ስልጠና ተሰጥቶል፡፡ ለሣይንስ እና ኢንጂነሪንግ ተመራማሪዎች  ለሞዴሊንግ እና Computing የሚያገለግለው Matlab ሶፍትዌር (Modeling and two dimensional drawing) ላይ በማተኮር ስልጠናው 128 ተሳታፊዎች በተገኙብት  ስልጠናው ተከናውላል፡፡

ስለሰተሰጠው ስልጠናና ወደፊት ተመሳሳይ ስልጠናዎችን በተቀናጀ መልኩ ለማዘጋጀት እንዲረዳ የተሳታፊዎችን አስተያየት ለመግኘት Quqtionnqries በማዘጋጀት ለመሰብሰብ ተሞክራል፡፡ የተገኘው ግብረ መልስ እንደሚያሳየው ሰልጣኞች በስልጠናው አሰጣጥና ጠቀሚታ መርካታቸውን አመልክተዋል፡፡




ለተመራማሪዎች የመረጃ አያያዝና አጠነቃቀር ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት

5. ለምርምር የቴክኒክ እና የመስክ ረዳቶች የመረጃ አያያዝና ማጠናቀር ላይ በተያዘው የስልጠና እቅድ በድምሩ ለ 65 ሰልጠኞች የተሰጠ ሲሆን፤ ሰልጠኞችም ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ ናቸው፡፡
6. በቶኒ ፋርም ለረዥም ጊዜ ላገለገሉና ለተቀረው ሰራተኛ ምሳሌ ይሆናሉ ለተባሉ የተመረጡ ሰራተኞች የምስጋናና የማበረታቻ ሽልማት ተደርጓል:: በዕለቱም ከሰራተኞች ጋር የውይይት ጊዜ የነበረ ሲሆን ሰራተኞች ቅሬታቸው እና ደስታቸውን ለመግለፅ ችለዋል፤እንዲሁም ውይይቱና ማበረታቻው ለወደፊትም እንዲቀጥል ጠይቀዋል::






**ግብ 9፡ የምርምር ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ማዘመን**

**ውጤት፡ የተስፋፋና የተቋቋመ ፋሲሊቲ**

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. በዚህ አመት የጠብታና የርጭት መስኖ ስራን በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ሰርቶ ለማሳየት በተደረገው ጥረት ¼ ሄክታር ቦታ ላይ ስራው ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኖአል፡፡




የርጭትና የጠብታ መስኖ ሙከራ ስራ በተግባር

2. በድሬደዋ ምርምር ጣቢያ የከርሰምምር ዉሃ የማበልጸግ ስራ ለመስራት በታቀደው መሰረት ስራው የተጀመረ ቢሆንም፤ ሰራውን ለመስራት የወሰደው ተቋም የአቅም ውስንንት ስለነበረበት ውሉ ተሰርዞ ለሌላ ለመስጠት አስፈላጊው ቅደመ ሁኔታ የተጠናቀቀ በመሆኑ፤ የከርሰ ምድር ውሀው ጥናት ግዜ ስለፈጀ በወቅቱ ሊጠናቀቅ አልቻለም፡፡
3. በግራዋ የምርምር ጣቢያ አጥር፤ የጥበቃ ማረፊያ፤ የድንች መጋዘን ለመስራት በተያዘው እቅድ መሰረት አንድ አስር በአራት ሜትር ስፋት ያለው ቤት ተሰርቶ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆኖአል፡፡ በዚሁ መሰረት የምርምር ምርቶቹን በሚፈልግበት የጥራት ደረጃ እንዲቀመጡና ለዘር ዝግጁ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፤፤



በግራዋ የተሰራው የድንች መጋዘን እይታ በከፊል

4. በኤረር ምርምር ጣቢያ አጥር ለማጠር እቅድ የተያዘ ቢሆንም፤ በዩኒቨርስቲውና በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት መካከል የተደረሰው ስምምነት ተግባራዊ መሆን ባለመቻሉ የምርምር ጣቢያውን ለመረከብ አልተቻለም፡ ፡ ስለሆነም የታቀደው ጣብያውን የማጠር ስራ ሊተገበር አልቻለም፡፡

5. ለቨርሚኮምፖስት ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተፈጥሮ ማዳበሪያን ለማምረትና ለማስተማሪያነት ለመጠቀም በተያዘውን እቅድ መሰረት፤ ስራውን ለማከናወን የሚሆን ቦታ የተገነባ እና ለስራ ዝግጁ የሆነ ሲሆን የሚቀረው ስራ ቦታዎቹን ተጠቅሞ ምርቱን በማምረት ለትምህርት፤ ለምርምርና ገበሬዎችን ለማሰልጠን መጠቀም ነው፡፡



ለቨርሚኮምፖስት ቤት እድሳትና አደስ እየተሰራ ያለ

## 5. የክትትል፤ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት

የምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በስሩ ያሉ ዳይሬክተሮች እንዲሁም የምርምር ትኩረት መስክ መሪዎች የታቀዱት ተግባራት በእቅዱ መሰረት ስለመሰራታቸውና መከናወናቸው ስርዓት ዘርግቶ (በሪፖርቶች፣ በውይይት መድረኮች፣ በመስክ ጉብኝቶች፤ በግምገማዎችና ሌሎች አስፈላጊ ዘዴዎች) ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እርምጃ ይወስዳል፡

### 5.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- ተመራማሪዎች በወቅቱ የሰሩትን ሪፓርት በአግባቡ እና ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ አለማቅረብ፡፡
- ተመራማሪዎች ምርምርን እንደ ዋና ስራ አለማየትና ለስራው ትኩረት አለመስጠት፡፡
- ተወዳድረው የምርምር በጀት አሸናፊ የሆኑ መምህራን ስራቸውን በወቅቱ አለመጀመርና በወቅቱ አጠናቆ የምርምር ውጤታቸውን ለምርምር ቢሮ አለማቅረብ፤፡
- ተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን ጠቃሚ በሆነ መልኩ ለተጠቃሚ የሚቀርብበትን ሁኔታ አለማመቻቸት፡፡
- ለምርምር የትኩረት አቅጣጫ መሪዎች ቢሮዎች፤ የጸሀፊዎች እና አስፈላጊ ሁኔታዎችን አለማመቻቸት፡፡

5.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

- ተከታታይነት ያለው ምክርና አስተዳዳራዊ እርምጃ መውሰድ፤፡
- ስራዎቻቸውን በአግባቡ እንዲሰሩ በመስክና በስራ ቦታ ክትትል ማድረግ፡፡
- የምርምር ስራዎችን በወቅቱ እንዲጀምሩ ማሳሰቢያ መስጠት፡፡
- ከዩኒቨርስቲው የበላይ አመራሮች ጋር በመሆን የቢሮ ውስጥ መማላት የሚገባቸው ቁሳቁሶች እነዲማሉ ማድረግና እና አስፋላጊ ቁሳቁስ እንዲማላ ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡

በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት ስር ለ2008 ዓ.ም የአራተኛው ሩብ አመትና የአመቱ እቅድ ክንውን

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያ ዊ ግቦች | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያ ዊ ግቦች | የግ ቡክ ብደ ትበ መቶ ኛ | ከስትራ ቴጂያዊ ግቡ የሚጠበ ቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ ክንውን | | | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 4ኛ | ክንውን | ክንውን በ (%) | እቅድ | ክንውን | ክንውን በ (%) | |
| የተገልጋይ/ደንበኛ/ባለድርሻ አይታ | የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና እርካታማ ሳደግ | የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና እርካታማ ሳደግ | 10 | ያደገ የባለድርሻአካላት ተሳትፎ እና እርካታ | ዓመታዊ የገበሬዎች እና ሌሎች የልማት አጋሮች የመስክ ቀን ማካሔድ | የመስክ ቀን ብዛት | 8 | 0 | 2 | - | 8 | 10 | 125 | |
| | | | | | የደንበኞችና የባለድርሻ አካላት የቴክኖሎጂ ፍላጎት ዳሰሳ በተለያዩ ወረዳዎች ላይ ማካሄድ | የወርዳዎች ብዛት | 10 | 0 | 0 | - | 10 | 14 | 140 | የጨመረ የደንበኛ የቴክኖሎጂ ፍላጎት |
| | | | | | በማህበር የተደራጁ ሴቶችን የተክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ | የማህበር ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 100 | 2 | 2 | 100 | |
| | | | | | የሴቶችን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማጎልበት | ከተሳታፊ ዎች በመቶኛ | 10 | 10 | 10 | 100 | 10 | 10 | 100 | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | አጋርነትን ና ትስስርን ማሳደግ | የምርምር አጋርነትን ና ትስስርን ማሳደግ | 10 | ያደገ አጋርነት ና ትስስር | ምርምር የሚሹ ችግሮችን ከበለድርሻ አካላት ጋር መለየት፤ንድፈ ሀሰብ መቅረፅ | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 3 | 300 | |
| | | | | | አዳዲስ ዘር አምራች ማህበራትን ለዘር ብዜት ስራ ማዘጋጀትና ማደራጀት | ቁጥር | 4 | 0 | 0 | 0 | 4 | 4 | 100 | |
| | | | | | ነባር ዘር አምራች ማህበራትን ዘር በጥራት ያመርቱ ዘንድ መከታተልና መደገፍ | የማህበራት ቁጥር | 42 | 0 | 0 | 0 | 42 | 42 | 100 | ተከታታይነት ያለው ስራ በመሆኑ |
| | | | | | ከኢንደስትሪዎች ጋር የምርምር ትብብር መፍጠር | ቁጥር | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 3 | 75 | |
| | | | | | ለ2009ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን ለውድድር መጋበዝ | የጥሪ ቁጥር | 1 | 0 | 0 | - | 1 | 1 | 100 | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ለ2009 ዓ.ም ለውድድር ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ የምርምር ንድፈ ሃሣቦች የሚቀርቡበት መደረክ ማዘጋጀት | የመድረክ ቁጥር | 6 | 6 | 6 | 100 | 6 | 6 | 100 | ሁለተኛ ዙር ግምገማ በቅርብ ካሂዳል |
| | | | | | 33ኛ አመታዊ የምርምር እና ስርፀት ጉባኤ በስድስቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ማካሔድ | ቁጥር | 1 | 0 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ ኮንፈርነሶችን ማካሂድ | የኮንፈረነስ ቁጥር | 3 | 2 | 2 | 100 | 4 | 6 | 150 | ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ጋር በመተባበር የተሰራ |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | ፍላጎት ተኮር የመማር ማስተማር ፤ የምርምር ውጤቶች ና አገልግሎ ቶችን ማሳደግ | ፍላጎት ተኮር የምርምር ውጤቶች ን ማሳደግ | 25 | የጨመረ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ የቴክኖ ሎጂ ውጤቶች | የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅና ማላመድ | የቴክኖሎጂ ቁጥር | 40 | 10 | 23 | 230 | 40 | 53 | 132.5 | በአብዛኛው አፍ ቲ ሲዎችን በመጠቀም የተሰራ |
| | | | | | ለዘር አምራች ማህበራት የድንች ዘር ማከማቻ መገንባት | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | የሚገነባበት ቦታ በጉልበት ስራተኛ ባለመገኘቱ |
| | | | | | የዘር ብዜት ስራ | በሔክታር | 60 | 20 | 13 | 65 | 60 | 66 | 110 | |
| | | | | | ጥራቱ የተመሰከረለት ዘር እንዲመረት ማድረግ | በኩንታል | 1000 | 0 | 0 | 0 | 1000 | 1120 | 112 | |
| | | | | | የተሸሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ማባዛት | ቁጥር | 50 | 10 | 0 | 0 | 50 | 40 | 80 | |
| | | | | | የተሸሻሉ ፍየልና በግ ዝርያዎችን ማባዛት | ቁጥር | 200 | 50 | 50 | 100 | 200 | 200 | 100 | |
| | | | | | የተሸሻሉ የስጋ ከብት ዝርያዎችን ማባዛት | ቁጥር | 10 | 2 | 5 | 250 | 10 | 13 | 130 | |
| | | | | | የእናት ንብ ማባዛት ስራ በሐረማያ የንብ ጋጣ መስራት | ቁጥር | 6 | 3 | 0 | 0 | 3 | 3 | 100 | |
| | | | | | በስድስቱ የምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች ንኡስ ትኩረት አቅጣጫዎች የምርመር ቡድኖችን ማዋቀር | የምርመር ቡድኖች | 22 | 0 | 0 | 0 | 22 | 22 | 100 | |
| | | | | | በዩኒቨርስቲው የበጀት ድጋፍ በስድቱ የምርምር | ፐርሰንት | 100 | 25 | 25 | 100 | 100 | 100 | 100 | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የትኩረት አቅጣጫ የሚካሄዱ 348 ምርምሮችን መከታተልና መደገፍ | | | | | | | | | |
| | | | | | በኢትዩጵያ ግብርና ምርምር ኢኒስቲቲዩት ድጋፍ የሚካሄዱ 113 ምርምሮችን መከታተልና መደገፍ | ፐርሰንት | 100 | 25 | 25 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | | በስድቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫ የሚካሄዱ ምርምሮችን ማጠናቀቅ | ቁጥር | 100 | 33 | 20 | 60.6 | 100 | 66 | 66 | ተመራማሪዎች ሪፓርታቸውን ወደ ምርምር ቢሮ ያላስገቡ በመሆኑ እንጂ የታቀደውን ያህል እንደተሰራ ይታመናልለ፡ |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | የምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና ህትመት ማሻሻል | 15 | የተሻሻለ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሽራዎችና የምርምር የህትመት ውጤቶች | የተለያዩ ዘሮችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት | በኩንታል | 1200 | 800 | 500 | 62.5 | 1200 | 1320 | 110 | በዝናብ እጥረት ምክንያት ተጠቃሚዎች ቁጥር ሰለጨመረ |
| | | | | | በትግበራ ላይ ያሉትን ቴክኖሎጂዎችን በእግዚቢሽን ማስተዋወቅ | ቁጥር | 2 | 0 | 3 | 0 | 2 | 5 | 250 | ምቹ አጋጣሚዎችን በመጠቀም የተከናወኑ፡፡ |
| | | | | | የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች መድረስ | የማዕከላት ቁጥር | 40 | 15 | 15 | 100 | 40 | 40 | 100 | |
| | | | | | ለወረዳ ሙያተኞች፣ ለልማት ሰራተኞች፣ ለአርሶ አደሮችና ሌሎች ባላድርሻ አካላት በግብርና እና ሌሎች መስኮች ስልጠና መስጠት | የስልጣኞች ቁጥር | 850 | 300 | 100 | 33.3 | 850 | 650 | 76.5 | |
| | | | | | የ2014/15 (32ኛ) የምርምርና ስርፀት ፕሮሲዲንግ ህትመትን ማጠናቀቅ | ቮሊዩም | 3 | 0 | 0 | 0 | 3 | 3 | 100 | |
| | | | | | የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር | ቁጥር | 12 | 4 | 2 | 50 | 12 | 10 | 83.3 | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መጣጥፎችን (articles) በሚገመገሙ (Peer-reviewed) ጆርናሎች እንዲታተሙ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | | | | | | | | | |
| | | | | | የዩኒቨርሲቲውን ጆርናሎች የተለያዩ ቮልዩሞችናእትሞች ማሳተም | ቁጥር | 4 | 2 | 0 | 0 | 4 | 4 | 100 | |
| | | | | | የምርምር ፖሊሲና የተለያዩ መመሪያ ሰነዶችን ማሳተም | ቁጥር | 3 | 1 | 1 | 0 | 3 | 1 | 33.3 | በፕሮግራም መደራረብ ምክንያት ስራዎች ባለማለቃቸው |
| | | | | | ከተመራማሪዎች በቀረበ የምርምር እይታ ምርምር እያካሄደ ሣይንሳዊ ጽሁፎችንና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብ | መጣጥፍ | 10 | 5 | 0 | 0 | 10 | 32 | 320 | ምቹ አጋጣሚዎች በመፈጠራቸው ምክንያት 6 በአዲሰ አባባ ጤና ነክ እን 22 በሐረማያ ግብርና ነክ ሳይንሳዊ ጽኁፎች ቀርቧል |
| | | | | | የምርምር ሥራዎች እና የምርምር ውጤቶችን የሚያስተዋውቁ በራሪ ጽሁፎችን፣ ፖስተሮችን ባነሮችን፣ መጽሄቶችን፣ ሚኒ ሚዲያዎችን እንዲሁም የሬዲዮና የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ማሰራጨት | የማስተዋወቂያ ፅሑፎች | 6 | 2 | 4 | 200 | 6 | 11 | 183.3 | ሳምንታዊ የሬድዩ ፕሮግራም በተከታታይነት እየተሰጠ ይገኛል፣ ምቹ አጋጣሚዎች በመፈጠራቸው ምክንያት ሳይንሳዊ ጽሁፎችን በበራሪ ወረቀቶች ለማስተላለፍ ተሞክሮአል፡፡ |
| | | | | | | | | 1.0 | | | | | | |
| የፋይናንስ/የበጀት እይታ | ገቢ ማሳደግና የገቢ ምንጮችን | የምርምር ድጋፍ ምንጮችን (research | 9 | ያደገ የምርምር ድጋፍ ምንጮች | የምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶችን የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ማስቻል | ብር በሚሊየን | 1.5 | 0 | 1.0 | 0 | 1.5 | 2.55 | 170 | |
| | | | | | ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የምርምር ድጋፍ ማግኘት | ብር በሚሊየን | 1.2 | 0.6 | 0.6 | 100 | 1.2 | 1.2 | 100 | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማስፋት | funds) ማሳደግ | | | ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር የምርምር ድጋፍ ማግኘት | ብር በሚሊየን | 10 | 2.5 | 2.05 | 82 | 10 | 14.05 | 140.5 | በየ ሩብ አመቱ ድጋፍ ሰጪ አካላት የለቀቁት ለምርምር የሚሆን በጀት ነው፡፡ |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | የሐብት አጠቃቀ ምን ስልጠት ማሳደግ | የሐብት አጠቃቀ ምን ስልጠት ማሳደግ | 5 | የተሳለጠ የሀብት አጠቃቀ ም | የምርምር ፈንዶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን መከታተል | የግምገማ ቁጥር | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | |
| | | | | | የመስክ ጉብኝትና ክትትል | ቁጥር | 12 | 3 | 3 | 100 | 12 | 12 | 100 | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| የውስጥ አሰራር ሂደት እይታ | የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳለጥ | የስራ ሂደቶችን ቅልጥፍናና ስልጠት ማድረግ | 11 | የተቀላጠፈና የተሳለጠ የስራ ሂደቶች | የመወሰን ዓቅምን ማሳደግና ያልተማከለ አሰራርን ማስፈን | የውይይት መድረክ | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | |
| | | | | | የምርምር ትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ የንዑስ ትኩረት መስኮችንና የምርምር ቡድኖችን ማዋቀርና መልካም አስተዳደርን ማስፈን | ቁጥር | 6 | - | - | 0 | 6 | 6 | 100 | የምርምር ትኩረት መስኮችን ያማከለ ቡድኖች የተዋቀሩና እየተንቀሳቀሱ ሲኖን፤ ከዚህም መልካም ተሞክሮዎች እየተገኙ ይገኛል፡፡ |
| | | | | | የስራ ላይ ስልጠና መስጠትና | የሰልጣኝ ብዛት | 40 | 10 | 10 | 100 | 40 | 40 | 100 | በስራ ላይ ያሉ ሀላፊዎችን በስራ ሂደት ላይ፤ ስለ አጋጠሙ ችግሮች እና አፈጻጸም ውይይት ተደርገዋል |
| | | | | | መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የልማት ሰራዊት መገንባትና መከታተል | የልማት ሰራዊት ብዛት | 20 | - | - | - | 20 | 20 | 100 | በየአስራ አምስት ቀኑ እየተገናኙ የሚወያዩ ሲሆን ከውይይቱም ስራን |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | የሚያፋጥኑ እና ችግሮችን የሚፈቱ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| የመማማርና ዕድገት እይታ | የሰራተኛውን አቅም መገንባት ፣ መሳብ፣ ማነቃቃት ፣ ማቆየት | የአመራር ብቃትንና ተነሳሽነትን ማሳደግ | 5 | ብቁና ተነሳሽ አመራር | የአመራር ስልጠና መስጠት | የሰልጣኞች ብዛት | 12 | 0 | 17 | 0 | 12 | 17 | 141.7 | ሁለት የማእከል አስተባባሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች በስልጠና ውስጥ ስለተካተቱ |
| | | | | | የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ማድረግ | የተሳታፊ ብዛት | 10 | 0 | 1 | 0 | 10 | 18 | 180 | በሀገር ውስትና ከሀገር ውጭ የተለያዩ ልምድ ለውውውጦች የተደረጉ ሲሆን፣ መልካምለ ልሞዶች ተገኝተውበታል፡፡ |
| | | | | | ለመምህራን የምርምር የንድፈ ሃሣብ አዘገጃጀት ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 60 | 30 | - | 0 | 60 | 103 | 171.7 | ምቹ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ምክንያት |
| | | | | | የመረጃ አያያዝና ትንተና ስልቶች ላይ ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 120 | 60 | 33 | 55 | 120 | 128 | 107 | |
| | | | | | የሳይንሳዊ መጣጥፍ (Paper) አዘገጃጀትና የውጤት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 40 | 20 | 50 | 250 | 40 | 91 | 228 | ምቹ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ምክንያት |
| | | | | | ለምርምር የቴክኒክና የመስክ ረዳቶች በመረጃ አያያዝና አጠናቀር አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት | ብዛት | 80 | - | - | - | 80 | 65 | 81.3 | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋት | የምርምር ፋሲሊቲዎችን | 10 | የተስፋፋና የተቋቋመ | የጠብታና ስፕሪንክለር መስኖ ቴክኖሎጂ በራሬ የምርምር ጣቢያ መስራት | ሔክታር | 1 | - | - | - | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | በድሬደዋ ምርምር ጣቢያ | የውሃጓድ | 3 | - | - | - | 3 | 0 | 0 | በስራ ላይ ያለ እና |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ና ማዘመን | ማስፋፋት ና ማዘመን | | ፋሲሊቲ | የከርሰምምር ዉሃ የማበልጸግ ስራ መስራት | ውሃ ቁጥር | | | | | | | | ያለተጠናቀቀ ነው፡፡ |
| | | | | | በጉራዋ ምርምር ጣቢያ አጥር ማጠር | ሜትር | 500 | - | - | - | 500 | 500 | 100 | |
| | | | | | በግራዋ የምርምር ጣቢያ የጥበቃ ማረፊያ ቤትና የድንች መጋዘን መስራት | በፐርሰንት | 100 | - | - | - | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | | በድሬደዋ ምርምር ጣቢያ የስራተኞች ቢሮ መስራት | ፐርሰንት | 100 | - | - | - | 55 | 30 | 54.5 | መሰረት ድንጋይ ተሰርቶአል |
| | | | | | በኤረር ምርምር ጣቢያ አጥር ማጠር | ሜትር | 500 | - | 0 | 0 | 500 | 0 | 0 | በዩኒቨርስተው ና በሐረሪ ህዝብ ብ/ክ/መንግስት መካከል የተደረሰው ስምምነት ተግባራዊ ባለመሆኑ ምክንያት፡፡ |
| | | | | | ለቨርሚ ኮምፖስት ቴክኖሎጂ የሚውል መጠለያ መስራት | ቁጥር | 1 | - | - | - | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | | | | | | | | | | |